# አዲሱ የልመና ሚኒስትር!

(ጭውውት)






ከሚስጥር ኪሴና ከእናቱ መቀነት- በሚያገኘው ሸልንግ

ልጀ ሰይፈ ፋንታ- ልክ እንደ አገሬው ወግ

ጥሩ አርጎ አሳዳገው -ቀንዳሙን ዳሌ በግ።

ሙከቱን ሳናርደው- ወይም ሳንሸጠው

ደርግ የአገሬውን ሰው- በመትረይስ ሲያጭደው

ልጀ ሸፈተና- ኢህአሠ ወስጥ ገብቶ

ድፍን ዓመት ቆዬ- ውጊያው ተበራቶ።

በረሃ ቆይቶ- ጎንደርና ጎጃም - ትግራይም ገስግሶ

ልጀ ሰይፈ ፋንታ- ወልዲያ ተመልሶ

የጀግና አቀባበል- ላደርግ ወሰንኩና

መሸትሸት እንዳለ- ሙከቴን አርጀ

ጠዋት አነጋግ ላይ-ቆዳውን እንዲሸጥ- ሰጠሁት ለልጀ

ከቤታችን ማዶ- ያለውም ነጋዴ- ቆዳውን አየና

ከልጀ ወሰደው- ሰባት ብር ሰጠና።

ከወልዲያ ደሴ- ከደሴ ኮምቦልቻ- ከኮምቦልቻም ሸገር

ከሸገር ጅቡቲ- አርጎ በቀይ ባህር

ተሻግሮ ውጭ አገር- ቆዳው ተሸጠና

በአማሪካ ምድር- የአባ ፋንታ ቆዳ- እጅግ ከበረና

የሳልሞን ቸዝ ምስል- የአብርሃም ሊንከን

ላዩ ላይ ተስሎ- አለና ሽቅረቅር

መዳፍ -መዳፍ ያክል- ሆኖ ተቆራርጦ- ሆኖ በብዛት

ተብሎ ተከትቦበት- “ህጋዊ ገንዘብ ነው- የአሜሪካ ሃብት”

ሚሊዮን መቶ ሺ...

ሃምሳ፤ መቶ ና ሽህ- ላዩ ላይ ተፅፎ

ካዝና ውስጥ ገባ- በጥብቅ ተቆልፎ።

ልጄም ከኢህአሠ- መስማማት አቅቶት

መንገዱን አቀና - ሊገናኝ ከተሃት

እዚያም ሳይሳካ ድርቡሽ አገር ገብቶ- አመት እንደቆዬ

አማሪካ ገባ- አለኝ እሱን ያዬ።



አመታት ነጎዱ- የእኔም ልጅ ተማረ- በሰላቶ መምር

የምጣኔ ሃብትን- የሚያስችል ምርምር

ከዚያም ባንክ ገብቶ- ስራ ጀመረና

ለጥቂት ዓመታት- ያሳደገውን በግ- ቆዳ ቆጠረና

የምስር የድርቡሽ- የነጭ ምትሃት- ተሃትን ወንድ አርጎ

መንግስት ሲገለብጥ- ሰይፈም ሰበብ አርጎ

ከዲ ሲ ተሳፍሮ- ኢትዮጵያ ገባና

የመለስ አገልጋይ- መሆን ወሰነና

“ኤክስፐርት” ተብሎ- ትልቁ ካቢኔ

ሲለምን ሰማሁት- ይኸው አየሁ ባይኔ።

የዝያን ዳሌ በጌን- የከበረ ቆዳ

ማስገኘት የሚያስችል- ለአገሪቱ በእዳ

አልያም ለምፅዋት- ብልሃት ፍለጋ

ሊሰራ የእኔ ልጅ- አገር የሚጎዳ

ዛሬ መለስ ሾመው -ሚኒስትር ነህ አለው

የሸጠውን ቆዳ- ለማኝ አደረገው።

ዳግማዊ ዳዊት
Ethio_dagmawi@yahoo.com
መስከረም 2003 ዓ.ም.